ሸክም

አና

ፍቅር

የጥተም ስብስብ

by

betelehem tefera

ምስጋና

ባለመቻሌ ውስጥ ሆኜ የምታስችለኝ አምላክ ሆይ የስጋዬ የነፍሴ ባለቤት ሁል ጊዜ በመቻልም ባለመቻል ውስጥ በውድቀትም በከፍታም ጊዜእንዳመሰግንህ ስለረዳሽኝ አመሰግንሃለው

አንተን ለማመስገን እስትንፋስ ይበቃልና አመሰግንሃለው አለመቻሌን የቻልኩት ባንተ ነውና አመሰግንሀለው

ርእስ

የምር የምቃዠው 1
ጥያቄ ነው 3
አሁን ነበር 6
ፍቅርን ሳፈቅር 9
ያልገባን ክርስቶስ 11
አዎ እንትን ነኝ 13
እንደገና 15
ሱሰኛሽ 17
እየሱስ ሰው ሲሆን 19
ሰው መሆን ሀጥያቱ 21
የነፍስ ፆታ 23

ፍጡር ለፈጣሪ 25
ዝም ያለ ዝምታ 1 26
ዝም ያለ ዝምታ 2 27
እናትየው..29
ዝምታ ሲጮህ 31
ሸክም እና ፍቅር 32
አትብላ..34
አዝኜ ሳበቃ 36
ሀሳበ ሀሳብ..38
ሸክሜ ከብዶኛል...40
ከመኖር ባሻግር...41
በልጄ ውስጥ ያለችው እናቴ 43
ምረጭ አትበሉኝ 46
አፈርኩልህ...49
ሰውረኝ 51
አጠይቁኝ...53
ሙሽራዬ..54

የምር የምቃዡው

ቀኔ መባክን ነው ቅዠት ነው ምኞት

ታትሮ መፈለግ ከንቱ መቃተት

ቀኔ ሀሳብ ብቻ ጥበቃ ናፍቆት

መገፋት መታገስ የለውም ህይወት

ቀኔ ረሀብ ነው የማይረካ ጥማት

ተስፋን ሲያሳድዱ ከዛሬ መጥፋት

ቀኔ ሰቀቀን ነው ፍርሀት ጭንቀት

ማይጨበጥ እውነት የማያልፍ ከርምት

በእኔ ቤት

ህይወት ምትጣፍጥ ፀሀይ ስትጠልቅ

ያይኔ ቆብ ሲከደን ከእዚህ አለም ስርቅ

የምድርን ጣጣ ራሷ ላይ ትቼ

በስጋ እንቅልፌ መንፈሴን አንቅቼ

የነፍስ ፍሰሃ ሀሴት አገኛለው

ከልካይ ሳይኖርብኝ ውስጤን እኖራለው

ህግ ነውና

መልሼ እንደገና

ጸሀይ ስትወጣ በአካል እነሳለው

የታይታ ህይወቴን እቀጥለዋለው

ጥያቄ ነው

ሀ ብዬ ልጀምር ሀ ሁ እንደገና

መሰረት የሆነ ጥያቄ ነውና

ደፍረትም አይደለ ከፋትም የለበት

ጥያቄ ብቻ ነው የሚያደርስ ከእውነት

እኔ

አሁን እና ያኔ እንቡጥ ነኝ ለእናቴ

ክብሬ አልወረደም ልእልቱ ለአባቴ

በብር ማይተመን ጊዜ የማሽረው

የተከፈለልኝ ዋጋዬ ውድ ነው

ዛሬ እኔም ደረስኩና

ባለእዳ ተረኛ ሆንኩና

ፅዋውን ቀመስኩኝ ለፍቅር አማጥኩኝ

ስለመውደድ ብዬ ራሴን ወለድኩኝ

እኔም እንደ እናቴ እማዬ ተባልኩኝ

ማንነቴን ሰጠው በፍቃድ ታሰርኩኝ

አዎ እናትነት ስጦታ ቢሆንም

ሽንፈቴን አምኜ ድካሜን ብወድም

ግን ግን ጥያቄ አለኝ

አለም የካደችው ውስጥ ውስጤን የሚያመኝ

እዚህ በእኛ መንደር ሴት ልጅ ስትጠራ

ከባሏ በኋላ የሚደርሳት ተራ

ትውልድ ለማስቀጠል በሰው በእንስሳቱ

ለህመም ሽክሙ የሚሰጣት ፊቱ

ትንሽ ዞር ስንል ስሚም ይረሳና

እሱ መጠሪ ነው እሷ ተሸፍና

ይህንን አውቅና ያንንም አይና

እብሰለሰላለው ስለምን እልና

በዚች የወንድ አለም ፈላጭ ቆራጭ ራሱ

የሴት እኔነቷ ለምን መደምሰሱ

በትውልድ ሂደት ውስጥ ህመሟ ብዛቱ

ከቁጥር መጉደሏ በየ ሀይማኖቱ

ከእንቁ ስትልቅ ምነው ደበዘዘች

መሪው እሱ ሆኖ ሳትመርጥ ተከተለች

አሁን ነበር

አሁን እኮ ነበር ከቤት የወጣውት

ትምህርት ፍለጋ ርቄ የሄድኩት

አሁን አሁን ነበር ስራ የጀመርኩኝ

ወላጆቼን ትቼ ብቻዬን የቆምኩኝ

አሁን ነበር አሁን ናፍቆቴን የቻልኩኝ

ተነጥዬ መኖር ማደጌን ያወኩኝ

አሁን አሁን ገና አንተን አገኘውኝ

በፍቅርህ ወደኩኝ ትስስር ፈቀድኩኝ

አሁን ነው የዳሩኝ ችቦ አይሞላም ብለው

እኛም እግር ስመን ጎጆ የቀለስነው

አሁን አሁን ወልዶ አመት ተከበረ

የፍቅራችን ቅሪት ውስጤ ተፈጠረ

አሁን እናት ልሆን ህመም አሳለፍኩኝ

ስቃዬን ረስቼ አይኔንም አየሁኝ

ትንሽዬ እንቡጥ ድጋፍ የምትሻ

ድረሱልኝ ምትል በምሬት ልቅሻ

በድዶችህ ስቀህ ደስታን ምታጠግበኝ

በአንገትህ ስር ሽቶ ሰላም ምትሰጠኝ

ልጄ ስጦታዬ

የህይወትን ትግል ድካሟን መርሻዬ

ከመቼው ተራመድክ ከመቼው ጎረመስክ

ድምፅህ ጎረነነ መቼ ጢም አበቀልክ

በብርሀን ፍጥነት ሁሉ ተለወጠ

የልጄ ልጅነት አሁን አመለጠ

ሳልጠግበው አደገ በፍቅር ተጠመደ

እኔን ትቶኝ ሊሄድ አንዲት ልጅ ወደደ

አሁን እኮ ነበር ልጄን የወለድኩት

ዳዴ የጀመረው ጡቴንም ያስጣልኩት

አሁን ነው የሮጠው ልጆች የገጠመው

አሁን ነው መክሬው ሰምቶኝ የታረመው

ልጄ እኮ አደገ በጥበብ በለጠኝ

ዘመን ሲምታታብኝ ከስህተት መለሰኝ

አሁን ግን ምንድነው የት ነው ትናንትና

ሁሉ ሀላፉ ነው በህይወት ጎዳና

ፍቅርን ሳፈቅር

ያሙን እንደዋለ ያሙን እንዳደረ

አንጀቴ ተራበህ በጥምህ አረረ

ስቅስቅ ያደርገኛል ሀዘን ነፍሴ ገብቶ

ያላገኘህ ልቤ አንተን ማጣት ፈርቶ

ግን አንተ ማን ትሆን እንዲህ ያበድኩልህ

በጠራራ ፀሀይ ውድቅት ምጠብቅህ

የአስቴር አወቀን ዘፈን እየሰማው

ስላንተ በምናብ ሰርክ ቃትታለው

በማየው ነገር ላይ አንተ ተስለህል

ቀልብና ሀሳቤን ወስደህ ሰውረሃል

ስጋዬ በድን ነው እኔ እዚህ የለውም

ዘመኔ ተጋምሶ አንተን ብቻ ሳልም

ግን አንተ

ስጋን አለበስክም በአካል አላውቅህም

በሚታየው አለም አልተመላለስክም

የጥበብ ስራዬ የምናቤ ፍጥረት

ውዴ ነህ ምኞቴ የወለደህ እምነት

ፍቅሬም ፍፁም ነው አይቀናና አይታበይ

ትእግስቱም ሰፊ በምግባሩ ሰናይ

ፍቅሬ ፍቅር ነው አለም የማያየው

ጊዜ የማይሽረው ለዘላለም ህያው

ያልገባን ክርስቶስ

ማን ነው ያሳደደው ማንስ ተከተለው

ማን ነው ደቀ መዝሙር ማንስ አሰቀለው

በቤተ መቅደሱ ማነው የነገደው

ያምላክ ልጅነቱን ማን ነበር የካደው

በየ ጥጋ ጥጉ ተሸሽገው ያሉ

በሀጥያት የጎደፉ ደግሞም የተጠሉ

ቃሉን ሰምተው ብቻ አምነው ተቀበሉ

አለምን ትተዋት እሱን ተከተሉ

ፍፁሙ ክርስቶስ ከሀይማኖት ሊያድነን

ወደ ተፈጥሮዋችን መርቶ ሊመልሰን

ሰው ሊያደርገን ነበር እኛን የመሰለው

ስለፍቅር ነበር የሞት ሞት የሞተው

የደም ላብ ያላበው ሲኦል የወረደው

እሱን አምነን ብቻ አካል እንድንሆነው

እኛስ

ስሙን እየጠራን ስራው ግን ከበደን

የገዛ ሀሳባችን ጠልፎ እየጣለን

በአንድ ክርስቶስ ስም መንገድ ተለያይተን

ብዙ ጎጆ ቀልስን አንድ ቃሉን መዘን

አዎ እንትን ነኝ

እንትና እባላለው ያንተን አትንገረኝ

ቤተሰቤም እንትን የነ እንትና ልጅ ነኝ

ሰፈሬም እንትን ነው የት ነህ አልልህም

አንተን ብቻ ልወቅ አልመረምርህም

እንትን ዘር ተጎታች ከየት ነው የመጣች

ከየትስ ተነስታ ወዴት ሀገር ገባች

እኔ ምን አገባኝ ጎሳ ቀበሌህን የምመረምረው

ዘመድ አዝማድህ ላይ ጥናት የማደርገው

እንኳን እንኳን ጆርባህ ፊትህ ይቀየራል

የሰው ልጅ ተጠንቶ እንዴት ይታውቃል

ሌላው ይቅርና የውጪ የውጪው

የገዛ ራሴን አልጨረስኩ አጥንቼው

እንዲሁ እየኖርኩ

ብዙ ትናንት አለፍኩ

ስንቴ ቃሌን ክጄ ኪዳን አጎደልኩኝ

ስነቴ አለው ብዬ ከራሴ ጠፋሁኝ

እንትና ነህ ብዬ ልገልጥህ ይቅርና

የራሴው ተፈጥሮ መቼ ገባኝና

ብቻ ሁሉን ተወው መንጋውን አትምሰል

እንትን ነው በማለት ፍርድም አትገምድል

እንትን ናት እትበለኝ ከእንትን አትመድበኝ

በቡድን ፈርጀህ ቆሜ አትቅበረኝ

እንደገና

ፎቶን እንደማየት ትናንትን መልሶ

የፈሰሰን ውሃ ከመሬት ላይ አፍሶ

የሸኙትን ወዳጅ ዛሬ እንደመናፈቅ

ትናንት ለቀበሩት ደርሶ እንደመንሰቅሰቅ

እየኖሩ ማለቅ የጠሉትን መድገም

ያለን አደባብሶ ያለፈውን ማለም

እንደገና መንገድ ዘንድሮም እንደ አምና

ልብን የሚሰውር አዲስ የለምና

ፀሀይም ፀሀይ ነች ጨረቃም ጨረቃ

ሁሉ ቢሞላላት ህይወት መቼ ስቃ

ፍለጋ የሄደን ያለፈን መጠበቅ

ለሊቱ እስኪነጋ የሞተን መናፈቅ

እንደገና ንጋት ንጋት እንደገና

የተኖረን ህይወት መገረብ ሆነና

ፀሀይም ልጥወጣ ሰማይ ተገፈፈ

የጨለመው ለሊት ተሸንፎ አለፈ

ሱሰኛሽ

ምን ምግብ ብበላ በያይነት አይነቱ

ከጥሜ ላረካ መጠጣቱ ከንቱ

ሁሉ ቢሞላልኝ አንቺ የሌለሽበት

ምንም ባዶ ኦና እኮ ናት ህይወት

ውዴ ማሬ የኔ ቃሉ አነሰው አቅም

የመውደዴን መጠን ስሜቴን አይገልፅም

ላፍቃሪ ሱሰኛሽ

አይንሽ ብቻ ፈዋሽ

የምትለቂው ጨረር ስጋዬን አስሶ

ልቤን ነው ሚነካው ከውስጥ ውስጤ ደርሶ

ሰላም የምሆነው ገነት የምገባው

ፀሀይ ምትወጣልኝ አንችን ሳገኝሽ ነው

ሱሴ

ለቅፅበት ስትርቂኝ ህይወቴ ጨለመች

አካሌ ገረጣ ነፍሴ ተጨነቀች

ውብ አለሜ ውዴ ምኖርልሽ ሱሴ

ብወድ ባፈቅርሽነው መዋረድ መርከሴ

ላንቺ ብቻ ሲሆን ክብሬን ረግጣለው

እኔ እኔን አልሆንም አቅሜን አጣለው

እየሱስ ሰው ሲሆን

ግራህን ሲመታ ቀኝህንም ስጠው

ይሄ ጠላትህን አፍቅረው ውደደው

ውድቀቱን አትመኝ ክፉውን አታስብ

ይቅርታህም የሁን ካንጀትህ ውስጥ ከልብ

ለሚገድሉህ ፀልይ መስቀል ተሸከም

የበደለህ እሱን አድርገው ወንድም

እየሱስ ሰው ሲሆን የሰበከን እውነት

የሚመራ እኮ ወደ ሰላም እረፍት

በአለም ከመጡ ነብያቶች ልቆ

አስርቱን ትእዛዛት በልቡ ጠብቆ

ንፁህ ፍፁም ሰው

ስጋውን የገዛ ፃዲቅ ቅዱስ ነው

ደቀመዛምርቱም ቃሉን ብቻ ሰምተው

ተው ያላቸውን እሱን አምነው ትተው

እውነቱን ተካፍለው ወደው ተከተሉት

የበኩር ልጅ ብለው ለአለም ሰበኩት

እየሱስ ሰው ሲሆን ምድር ተቀየረች

አምላክ ፈጣሪዋ ስጋ ለብሶ አየች

በምግባር ትህትናው ስራው ተደነቀች

በፍቅሩ ተገዝታ በሞቱ ታከመች

አንድ እውነት የሆነው

ራሱ እየሱስ ነው

አንድ ንፁህ ፍቅር

እስከ ሞት መቃብር

አንድ ፍፁም ሰው

ስጋን አሸንፎ አለምን ያዳነው

ስሙ ይጣፍጣል እየሱስ ክርስቶስ

አልፋ እና ኦሜጋ የነገስታት ንጉስ

ሰው መሆን ሀጥያቱ

በቃኝ መብሰልሰሉ ጠላቴን መግደሉ

ከልብ እያደሙ ወዳጅ ማስመሰሉ

በቃኝ ማከማቸት ያዩትን መሰብሰብ

ለአላፊ ለጠፊው ለቁሱ መንገብገብ

በቃኝ መሳቀቁ ምን ይመጣ ብዬ

ማላውቀውን ነገ ዛሬ ላይ ተንብዬ

በቃኝ መቅበዝበዙ ከንቱ መመኘቱ

የያዙትን ጥሎ የሰው መቀማቱ

ልታጠብ በውሃ ገላዬን ልቀድስ

ወደ ኤደን ገነት እንደ ኸረት ልፍሰስ

ሰውነቴን ልግዛ መልካም ፍሬ ላፍራ

እኔነቴን ልካድ በስምህ ልጠራ

ግን ቅፅበት ሳያልፍ ሀሳቤ ይበተናል

ደመነፍሴ አይሎ ስጋዬን ይበላል

እንደተራበ ሰው ጥፋት አድናለው

ለማይረካ ርሀብ ነፍሴን አረክሳለው

መለስ እልና መሀከል ላይ ሆኜ አሰላስላለው

ፍፅምና ለኔ አይደለም እላለው

ስጋዬም ላይነፃ ነፍሴም ላትቀደስ

ስወድቅ ስነሳ ስመላለስ ላልደርስ

ለምን ማማረሬ ለምን መሳቀቄ

ተፈጥሮዬን መውቀስ ስነሳ ወድቄ

ይልቅ መቀበሉ ከራስ መስማማቱ

ሰው መሆን ነውና ድካሙ ሀጥያቱ

መቀበል እውነቱን

ፈጣሪን ፍጥረቱን

ሰውነት ነውና

ህይወት እንደገና

ትንሽ ትንሽ ማደግ በሌላኛው መፍረስ

ስጋም ወደ አፈሩ ተለይቶ ከነፍስ

የነፍስ ፆታ

ነፍስን ከስጋ ለይተን

ህያውን ከአፈር አውጥተን

ስርአተ ፆታን ለአፍታ ዘንግተን

የሰው ሰውነቱን መንፈሱን አጉልተን

እስቲ እናስበው

ከራስ በላይ እንሞግተው

እንመርምር እንጠይቅ

መልሱን ሳንጠብቅ

ከስጋው ስትወጣ ከአካል ተለይታ

ምንስ ይሆን ይሆን የነፍስያው ፆታ

ወንዳ ወንድ ሴታ ሴት

ወይስ ቅይጥ አንድነት

አልያስ አልያስ ዳግም አለ ውልደት

ትንሳኤ ለስጋ የሚሻገር ከሞት

እኔም ምን አውቃለው

መላሽ በሌለበት ጥያቄ አቀርባለው

እስኪ እናስብበት

ከልካይ በሌለበት

ሀቅ ሀቁ ስጋችን ፆታ አለው

ተግባሩም የአፈር ግቡም የመሬት ነው

ነፍስ ግን

ለአንዲት አላማ አንድ አካል ሊለብስ

ልምምድ የወጣ ምድር ሚመላለስ

ስጋን ጥሎ ሚሄድ ስራውን ሲጨርስ

በአለም ቆይታው ከርሞ የሚከሰስ

ገሀነብ እሳቱ ገነት የተዋበ

ጭንቀት አመራምሮት አዳም ተጠበበ

ወይስ

ዝም ጭጭ ፀጥ ለጥ

ከእውነት አንዲት ነፍስ ላታመልጥ

ፍጡር ለፈጣሪ

ፈጣሪ

ሳለ በዙፋኑ ሳለ ከነ ግርማው

በፍፁም ዝመታ በሰላም እርጋታው

ሁሉ በሞላበት ሁሉ ባማረበት

ደስታ እና ርካት ምግብ በሆነበት

ጅማሬ በሌለው ፍጻሜ በሌለው ዘመን እየኖረ

አምሳያውን ወዶ አንድ እለት ፈጠረ

በእጁ ያበጀው ትንፋሽ ያካፈለው

ያ ሰው ማምለክ ነበር ስራው

ፍጡር

ሀሴት የሚያደርገው ነፍሱ ምትለመልም

ለአምላኩ ሲገዛ ጌታውን ሲያስቀድም

ማምለክ ተልኮው ነው ማምለክ ማንነቱ

ፈጣሪውን ሲያነግስ ምትሰምር ህይወቱ

ዝም ያለ ዝምታ 1

በድንቅ ተፈጥሮዬ ስደነቅ ስመሰጥ

ከብዙ ጥያቂ ከአእምሮዬ ማምለጥ

ዝም ፀጥ አይቶ እንደላየ ሰምቶ እንዳልሰማ

ተርቦ እንደበላ ደግሞ እንዳልተጠማ

ጭጭ ዝም ፀጥ

ዛሬን ብቻ ማድመጥ

አሁን እዚህ መኖር

አእዋፍ ሲዘምሩ በገናን መደርደር

ከሀቅ መስማማት በእውነታ መደመም

ለምን ለምን ብሎ ለምንስ መታመም

ከአለ ከሆነ ጋር መፋለም ድካም ነው

የተከሰተውን አምኖ መቀበል ነው

ከመጣ ከሄደው ካሁን እሰማማለው

እንዳትቀሰቅሱኝ እኔ ተኝቻለው

ዝም ያለ ዝምታ 2

ባዶ ራስ ቀል ራስ ጥያቄ የማያውቅ

ለምን የማይገባው መልስም የማይጠብቅ

ሀሳብ ያለቀበት ዝምታ የዋጠው

ከሚመጣው ይልቅ የዛሬ ሚደንቀው

አሁንን የሚኖር እስከ ግሳንግሱ

ተፈጥሮን በማፍቀር የመነነች ነፍሱ

እሱ እሱ ነው ንጉሱ

ፍፁም ያረፈለት ስጋና መንፈሱ

ዝም ያለ ዝምታ የሚያማልል ህይወት

ይማርካል አሉ በፀጥታው ውበት

መድሃኒትም አለው ሀሳብ ላሳበደው

ሀቅን የመጋፋት ትግል ላደደበው

ዝምታ ያድነው

ፀጥታም ያክመው

እስቲ ለአንዲት ቅፅበት ጭጭ ፀጥ እንበል

ከዝምታ ጎጆ ላፍታ እንጠለል

መንነን እንጥፋ እንሰወር ከአለም

ከውስጣችን ጠልቀን ነፍሳችን ይታከም

እናትየው

ገላዋን አጣጥባ በፎጣ አድርቃ

የማለዳ ጮራ ፀሀይዋን አሙቃ

ከጡቷ አጥግባ ደግሞም አስገስታ

አልብሳ ደራርባ ንፁህ ፍቅር ሰታ

በእቅፏ አሙቃ

በፍቅር አንደላቃ

ወደ ራሷ መልስ

በሀሳብ በምናቧ ብዙ ሲመላለስ

ከየቱ ልጀምር ከቡና ከቁርስ

ገላዬን ታጥቤ ልቀይራ ልብስ

መፃፌን ላንብበው ከአልጋዬ ተኝቼ

ወይስ ልነቃቃ ትናንትን ሰርቼ

የምወደውን ፊልም አሁን ልመልከት

ሙዚቃም አምሮኛል ይሞዘቅ ይጫወት

ወይስ ለወዳጄ መልእክት ልላክላት

በጣም ናፍቃኛለች ደውዬ ላዋራት

ደግሞ ጊዜ ልውሰድ ላስብ ላሰላስል

በጥበብ ልሞላ አሻራዬን ልጣል

ከማማው ወጥቼ ከሀሳበ ሀሳብ

ለአፍታ እንኳን ሳላርፍ ትንፋሽ ሳልሰበስብ

ማማዬ

የእኔ ሚጢጢዬ

ከእጄ ተኝታ እንቅልፏን ጨረሰች

እንደተቀመጠኩኝ ተነስታ አለቀሰች

ተራበች ጠገበች

ዳይበሩዋን ቀየረች

አካሌን አድከመች

መንፈሴን አከመች

» ከኢቫ ጋር »

ዝምታ ሲጮህ

እንባ እየረጨ ሙሾ እየወረደ

ስቅ ስቅ ስቅስቅ ለልብ የከበደ

ፊደል ያልገለጠው ውስጥን ያነደደ

የታሰረ እውነት ሞቶ የታረደ

የሚጮህ ዝምታ የሚያለቅስ ፀጥታ

ምድርን ያናወጠ እዬዬ ኡኡታ

ከተዘጋ አንደበት የሚፈስ ጫጫታ

ቃላት የማይገልጡት የመንፈስ ሁካታ

ዝምታ ሲጮህ ፍጥረት ይናወጣል

መንደር አይበቃውም አለም ይጨነቃል

ሰውነትን አልፎ ነፍስን ይገናኛል

ከሰማያት ወቶ ከጥልቁም ይወርዳል

ምስክር ዝምታው ያቆመው ጠበቃ

እሱን የከሰሰው አለቀለት በቃ

ሽክም እና ፍቅር

ያን እለት ያን እለት

ስጋሽ ስትከፈል ስትለብስ ህይወት

አንቺነትሽ ሞታ አፈር ትገባለች

ነፍስሽም ተረታ ክብርን ታጣለች

የእኔነት ፍቅርሽ ሚዛንም አይደፋ

ራስ ማስቀደምሽ ዝንታለም ይጠፋ

ሲታምሙ ታመሽ ቀድመሽ ትከስሚያለሽ

እኔነት የለሽም ጥላ ትሆኛለሽ

ስጋት ፍራት ደግሞ ምኞት ተስፋ

ማይት ስትናፍቂ ይቺ እለት አልፋ

ደግሞስ

ሁለመናቸውን እንዲሁ ስትወጂ

ፍቅራቸው ትኩስ ነው ኖረሽ አትለምጂ

ክልክልን ከልክለሽ ፍፁም ስትፈቅጂ

አይናቸውን ብቻ አይተሽ ስትረጂ

ከብደውሽ አያውቁም አታውቂም ሰለችተሽ

እስከ ጉድፋቸው በፍቅር ተቀብለልሽ

ህመማቸው ጠንቶ የሚያምሽ አንችን ነው

መድሀኒት ፈውስም ነው ጠረን ትንፋሻቸው

አዎ ስትቆሽሺ ጠረንሽ ለውጦ

ልጅ ልጅ ስትሸቺ እናትነት በልጦ

ሁለንተናዊ ነው የአካልም የነፍስ

ሸክም እና ፍቅር ከአንጀት የሚደርስ

አሁን አትችይም መሽነፍ መውደቅ

ቆመሽ ትሄጃለሽ ህይወትን እስኪያውቅ

አትብላ

አባት ሲከለክል ምክንያቱን ደብቆ

ልጅም ተሳሳተ ሊመራመር አውቆ

እንደ አምሳሉ ለሰራው ሰው

ማወቅ መጠበቡ መለየት ቢበጀው

እንደ እስትንፋሱ ቀድሞው ባካፈለው

ደግ አባት ነውና መልካሙን አይነፍገው

ግና

ሁሉን ያውቃልና

ጅምር መጨረሻው ከፊቱ ነውና

ይህንን አትብላ ብሎ ከለከለ

የአባቱን ትእዛዝ ይሰማል ስላለ

ልጅም መቼም ልጅ ነው

ምኞት ይገለዋል ስትከለክለው

ኗሳ

እሳቱን ሲነካ እጁን ሲያቃጥለው

መሳቱን ተረዳ ማወቁም ገደለው

አባትም አዘነ ሰለአንድያ ልጁ

ከጥፋት ሊያድነው ተዘረጋ እጁ

አዝኜ ሳበቃ

ከፈተና አልፎ ፈተና ሚጠብቅ

ያለፈውን ትናንት ዛሬ የሚናፍቅ

በብልጭታ ሳቁ እንባ እያፈሰሰ

ፍዳውን ሲበላ ዋጋው እያነሰ

በአለም ሳላቹ … ብሎ እየተቀሰ

ህመሙን ሊያስታግስ ህግ እያፈረሰ

ድካሙ ሳይጥለው ችግሩ ሳይበቃ

ሁሉ ጨልሞበት የእሱ ፀሀይ ጠልቃ

ህይወት ትሆን እውነት

ሀቅ ይኖር ወይ ከሞት

እንዴት ያነፃፅራረው

ህይወት አልገባችው ሞትንም አያውቀው

ዝም ብዬ ሳየው የድካሙን ጥልቀት

የፈተናው ክምር የሀዘኑ ስፋት

የሚኖር ይመስላል ሺ ዘመናትን

ካሳ የሚቀበል ብዙ ብድራትን

ሰው ያ ሰው

በድን የለበሰው

ርካታው የአፍታ

ደስታው ናት ብልጭታ

ለጭንቀት ስቃዩ አዝኜ ሳበቃ

ደግሞ አስረሳችው በትንሹ ስቃ

ሀሳበ ሀሳብ

እኔ ግን እላለው

የሰው ልጅ ራሱ መንፈስ እና ነፍሱ

አንዷት ሳትጎድል ከነክብር ልብሱ

መጠሪያ ስያሜ ህያው ማንነቱ

ሀሳብ ነው ተፈጥሮው ግብአት ሰሪቱ

መልሼ አስባለው አሰላስላለው

ሰውነትን ለብሶ ሰው መሆን ስቃይ ነው

ዘወትር ፍለጋ ሌተቀን ስደት

ነፍሳችን ከስጋ ላይፈጥር ውህደት

ደግሞ ሲያመጣብኝ መንፈሴ ሲነቃ

ስጋዬን ሳባትል ነፍሴ ተደብቃ

በንጋቶች መሀል ጨለማ እየሳልኩኝ

ወጋገን ብርሃኑን ተከልዬ አለፍኩኝ

ሀሳብ ሲሰፍርብኝ ናላዬን ሲያዞረው

ውስጥ ውስጤን ዘልቄ እፈላሰፋለው

ለጥያቄዬ መልስ ጥያቄ አቀርባለው

ለማይገባኝ እውነት ምክንያት ፈልጋለው

ተራራ ገፋለው ምንጩን እደፍናለው

አእምሮዬ ደክሞ ልቤን ፈትናለው

አሁን እና አሁን ህይወት ቅፅበት ሆና

ለምን እንዴት ብዬ እኔስ አጣው ጤና

ቢሆንልህ

ላለ እና ላለፈው ለመጣው ዝም ፀጥ

ወደድክም ጠላህም ከእውነታው አታመልጥ

አሁንን መቀበል ከምናብ ተስማምቶ

ያሸነፈ የለም ከህይወት ተሟግቶ

ሽክሜ ከብዶኛል

ከትናንት በስቲያ እችላለው ብዬ

ካንተ ተለይቼ ያባቴን ቤት ጥዬ

በመረጥኩት መንገድ ነጎድኩኝ ጠፋውኝ

በረርኩኝ ካልኩበት ከምኔው ወደኩኝ

የደረስኩኝ መስሎኝ ለካስ አልጀመርኩኝ

አሸነፍኩኝ ብዬ ስንቴ ተረታውኝ

አዎ አቅቶኛ ሽክሜ ከብዶኛል

ግሳዬ ምክርህ ቁጣህ ይሻለኛኛል

ሰርክ መንከራተት ማስመሰል ደክሞኛል

የአባቴ እቅፍ ረፍትህ ናፍቆኛል

ከመኖር ባሻግር

ስንት ዘመን አልፎ ስንተኛው ተተካ

ስንት ምኞት ከሽፎ የትኛው ተሳካ

የፈሰሰው እንባ ከጉንጭ ኮለል ብሎ

ትራስን አርሶ ማዲያት ከፊት ጥሎ

የዛለው ጉልበትስ ሀሳብ ያደከመው

ሌተቀን ሰቀቀን ምኞት የደቆሰው

ስንት እውነት ደብዝዞ ሳያብብ ከሰመ

ሊነጋ ያለው ለሊት ከምኔው ጨለመ

ከመኖር ባሻገር አየር ከመሳቡ

እህል ውሃ ቀምሶ ደግሞ ከመራቡ

ስንት ህልም ነበረ ደርሶ ያልተኖረ

ማር ብለው ሲቀምሱት ከሬት የመረረ

አለ እየተባል ሳይኖር ያለፈ

ደርሶ ሳይቀመስ ድንገት የረገፈ

ተሰፋ ሲያንሰራራ ከሩቅ እየታየ

አገኘውት ሲሉ ከርሞ እየተለየ

ከመኖር ባሻገር ያልተኖረ ህይወት

ደብዝዞ የጠፋ ያልጨበጡት እውነት

ስንት ደስታ ከስሞ ስንት ሳቅ ከሽፈ

በጥበቃ ብዛት ስንት ጀግና አለፈ

በልጅ ውስጥ ያለችው እናቴ

የተኖረ ልጅነቴ ታወሰኝ፡፡ ደስ የሚያሰኘው ዘመን ፊቴ ድቅን አለ፡፡ አንድም ቀን እኔ እኔን በመሆኔ ጥርጣሬ አድሮባችሁ አያውቅም፡፡ በተሰጠኝ ህይወት ፍርሀት እንዲሰማኝ አድርጋችውኝ አታውቁም ነበር ነበር አዎ ነበር፡፡ እንደምንጭ የጠራ እንደወንዝ በደስታ የሚፈስ ነፍስን የሚያፍነከንክን ልጅነት፡፡

እንዲሁ ያላንዳች ቅድመ ሁኔታ እና ምክንያት ተቀበላችሁኝ እንዲሁ ወደዳችሁኝ እንዲሁ በፍቅር በነፃነት ራስህን በመሆን አረሰረሳችሁኝ አለሜ ነበራችሁ እኔነቴ የተቀረፀበት አለሜ ራሴን ያገኘውትም የህይወቴ ትኩስ ምእራፍ የተቀረፀበት፡፡ ሰው ቅፅል የሌለው ሰው ብቻ ሆኜ ነበር በቤታችን ያደኩት፡፡

ለካ የውጪው አለም ሌላ ነበር ሌላ እኔ የማላውቀው ሌላ አለም፡፡ በእናንተ ፍቅር ተሸፍኜ ያላየውት አለም ተገለጠ አየሁ ተጋጨብኝ የገሃዱ አለም እውነታ ውስጤ ካለው ጋር ተፋለሰብኝ፡፡ ለካስ ሰው በሁለት ይከፈላል ሴት እና ወንድ ተብሎ ክፍፍሉ ድልድሉ ያንን ማእከል ያደረገ ነው፡፡ የተፈቀደ የተከለከለ የሚቻል የማይቻል ሴት እኮ ነሽ ወንድ እኮ ነኝ አትችይም እችላለው በቃ አለሙ የሚያዜመው ሌላ ነው ሌላ ዳንኪራ፡፡

እያደርም ተፈጥሮ ፍጹም አለመሆኗን በብዙ መልኩ አሳየችን ነገረችኝ ፈተነችኝ ደግሞም አስተማረችኝ አንዳንዴ እላለው ምንስ ብንበደላት ነው

ከልጅነት እስከ እውቀት በፈተና ላይ ፈተናን እየደራረበች መከራችንን ምታበላን፡፡ አንዳንዴም እላለው ሌላ ቀላል መንገድስ አታ ነው፡፡ ገና ከአስራአንድ አመት ጀምሮ የምታሳቅቀን የምታሸማቅቀን ልንረዳው በማንችለው ስሜት መለዋወጥ እንዲሁም የገፅታ መቀያየር የምታስጨንቀን ምንስ አድርጉ ነው የምትለን፡፡

እንደ ቃሉስ ብናየው ሄዋን ምን ያህል ብታጠፋ ነው ትውልድ የሚቀጣው፡፡ ደግሞስ እኔ ስለእሷ ምን አግብቶኝ የትስ አውቄያት፡፡ ይሁን ግን ለምንስ ይሆን ሸክሟ ሳያንሳት ደግሞ ያንን ለመረዳት የበቃ አዳምን መፍጠር መስራት ያቃታት፡፡ ሰለምንስ ያለምርጫ ለአገልጋይነት እና ለረዳትነት አበጀችን ልምንስ ዋጋችንን መዝና ክብርን መለገስ ከበዳት፡፡

ስለህይወት ስለትውልደ መቀጠል ሸክሙን ሙሉ በሙሉ ከትንሽ እድሜያችን ጀምሮ ያለ አንዳች ምህረት በጨቅላ እና መከራ በማይችለው ጫንቃችን ላይ ጫነችብን፡፡ ጭራሽ ራሷ ያሸከመችንን ጣጣ ለዘመናት እንደ ርክሰት እንዲታይስ ለምን ፈቀደች፡፡ ያለአንዳች ምርጫ ስለተሰጠን ማንነትስ ለምን እንወቀስበታለን አልመረጥንም እኮ አልፈለግንም እኮ የኛ መሻትም አይደለም እኮ ገና ክፉ ደጉን ሳንለይ ሳንበስል እኮ ነው የተጫነብን፡፡

ስጋ ለብሶ ለምን ብሎ የሚጠይቅ አእምሮ ተሸክሞ አለም ላይ መመላለስ እጅጉን ከባድ ነው፡፡ ግን ይቀጥላል ትውለድ እንደኾረት ሳይቋረጥ ይፈሳል በዚ ሄደት ውስጥ ሄዋን ለመስዋእት ትቀርባለች በአካል በመንፈስ በስሜት ትታመማለች ትፈተናለች እያለፈች ትተካለች፡፡ እየተካችም ታልፋለች፡፡

ይገርማል እኮ በዚህ ውስጥ የሚያበረታት ፍቅር ብቻ ነው፡፡ በተፈጥሮ ፍርድ ሁሉን በሰጠቻቸው ልጆቿ እማ ስትባል ያኔ ታገግማለች ሰው ትሆናለች ድካሟን ትረሳለች በፍቅር ታክማ ቆማ ትሄዳለች የስሜቷን መመሰቃቀል ያካሷን ህመም የአለምን ክፉት ረስታ ያላትን ሁሉ አብዝታ ትሰጣለች ፍቅር የሚያሸንፈው ያን ጊዜ ብቻ ነው፡፡

ውዷ ልጄ በአይኖችሽ ውስጥ የተኖረ ልጅነቴን አያለው ደግሞ እሳሳለው የኔን ህይወት እንድትደግሚ እያስተማርኩሽ ነው ብዬ እፈራለው፡፡ አዎ አካሌ ክፋዬ ነሽ መንገድሽን ልጠርግ እጠማለው፡፡ ዞሬ እናቴን አስባለው አንድም ቀን እሷን እንድተካ አላስተማረችኝም እኔን እኔ እንዳገኝ ብቻ ነበር የነገረችኝ ግና ከህይወት መስመር ላልወጣ ያላስተማረችኝን ትምርት ኖሬ ተማርኩ፡፡

ለውጥ አዝጋሚ ነው ብዙ ነገር በመቀየር ውስጥ ነው፡፡ እየተጓዝን እንተካካለን እየተተካናን እንጓዛለን እየተተካካን እናልፋለን፡፡

ምረጭ አትበሉኝ

እውነት የሰው ልጅ ሳይፈልግ ከመጣበት አለም ላይ ሲኖር የፈለገውን ሁሉ ማግኘት እንደምን ይቻለው ይሆን? በጣም በጣም ቀላል የሆነው የምግብ እና የመጠጥ መርጫዬን ማስከበር እችላለውን? ሁል ጊዜ ያለማቋረጥ ጣፋጭ ነገር መመገብ እፈልጋለው ያንን ማድረግ ፍላጎቴ ነው፡፡ ቡና ከጠዋት እስከ ሌሊት መጠጣት ውስጤ ነው፡፡

የስጋ ፍላጎቴን ያለገደብ መፈፀም እችላለውን? ስፖርት ብሎ ነገር ደግሞ ጠላቴ ነው በቴሌቪዥን መስኮት ከማየት የዘለለ ስሜት የለኝም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ስርአት እና ህግ ድግግሞሽ መታሰር መወሰን መከልከል መገደብ አልፈልግም፡፡ ነፍሴ ያንን አምርራ ትጠየፋለች ዳሩ ምርጫዬን አልኖርም፡፡

ይችን አለም መርጬ አልተቀላቀልኩም መርጬ ሰው አልሆንኩም ፆታዬ የፍላጎቴ ውጤት አይደለም፡፡ መልክ ቁመናዬን ውስጥ ልቦናዬን ወላጆቼን እህት ወንድሞቼን ሰፍር ሀገሬን እኔ መክሬ ወስኜ አላገኘውትም ለወግ እንኳን ያማከረኝም የለም፡፡ እጅግ በጣም ጥቂት ውስን ነገሮችን ስመርጥ ፍላጎት ምኞቴን ስፈልግ ደግሞ ሁሌም ስህተት ጥፋት በሽታ ይሆናሉ፡፡

ያልጣፈጠኝ ያልመሰጠኝ ያልተመቸኝን በአስገዳጅ ህግ ቀድሞ ጥሩ ልክ ተብሎ እንድቀበል ተወስኗል፡፡ እናስ የቱ ጋር ነው የኔ ፍላጎት የሚከበረው? የቱስ ጋር ነው እውነቴ ልክ የሚሆነው?

እዚች አለም ላይ ምርጫ ብሎ ነገር የለም አእምሮን አሳምኖ ጥያቄን አጥፍቶ አሜን አሜን ይሁን ብሎ ብቻ መቀበል ነው ። ሀቁ ይሄው ነው ለምን? እኔን ለምን ለምን? ማለት እስከነአንካቴው ያጠፋል። እባካችው አማራጭ በሌለበት ፍትሕ በማይታሰብበት ውሸት ሲደጋገም ሀቅ በሚሆንበት ፍላጎት በማይከበርበት አለም ስኖር ምረጭ ብላችው አታስጨንቁኝ። አስቀድሞ ተመርጫለው እኔ የመምረጥ ፀጋም ሀይልም መብትም የለኝም።

እኔ መምረጥ ብችልማ አስቀድሞ ስለምን በዚች ምድር ላይ ሰው ሆኜ እፈጠርስ ነበር። ስለምንስ እንደሰንሰለት ወደተቀጣጠለ የህይወት ጥልፍልፍ የድካም ትብታብ ውስጥስ እገባ ነበር። ምንም ባላስፈለገ ነበር ምንም ራሱ ምንም በሆነ ባዶ ኦና በሆነ ነበር። ነበር ብቻ ነበር

የሰው ልጅ አንዱን ችግር ሲፈታ ያልታለመ ያልታሰበ ሌላ ውጥንቅጥ እየፈጠረ አቀለልኩ ሲል አዲስ ችግር እየፈጠረ አለምን ብልጭልጭ አስጨናቂ መድረግ እያደረጋት ነው። ደረስኩ አገኘውት ያለው ስኬት ሌላ ችግር ይወልድለታል በቃ መልሱ ጥያቄ ነው።

ከመወለዳችን ከመፀነሳች ከመታሰባችን በፊት ግን የት ነበርን? የሰው ልጅ አንዱን ችግር ሲፈታ ያልታለመ ያልታሰበ ሌላ ውጥንቅጥ እየፈጠረ አቀለልኩ ሲል አዲስ ችግር እየፈጠራል።

ከመወለዳችን ከመፀነሳች ከመታሰባችን በፊት ግን የት ነበርን? እዛ ሁሉ ፍፁም ሁሉ ሰላም ነበር። ያ የተሻለ ስፍራ ነበር ምክንያቱም ያ አለመኖር

ነው። ፍፁም ፀጥታ ፍፁም ሰላም ፍፁም እረፍት። በመኖር ሁሉ ጅምር ሁሉ እንቆቅልሽ ሁሉ ድካም ነው። የምንኖረው የማይሞላ ጎዶላችንን ለመሙላል እንከናችንን እየሻራረፍን ወደ ፍፁምነት ለመጠጋት ነው ነገር ግን ፍፁምነትን ሳናይ እናልፋለን።

አፈርኩልህ

አንደበቶችህ ሳይከፈቱ ቃል ከአፍህ ሳይወጣ ሳትናገር ሳታወራ አውቄሀለው:: ሆኖም ምላሽን አልሰጠውህም እንዳልገባው አለፍኩህ:: ለካስ አይንህ እንደነገረኝ አላወክም መንፈስህ እንደተረከልኝ አልገባህም :: አፈርኩልህ ስለ ጥፋትህ አፈርኩልህ:: ያከበርኩህ ስለአንተነትህ አይደለም የማከብረው እኔነት እና ስብእና ስላለኝ ነው:: በጭራሽ ስለተገባህ እኮ አይደለም:: የሰውን ልጅ ሁሉ የሚያከብር ማንነት ስላለኝ ብቻ ነው::

አንደበትህ እንዴት ታዘዘልህ ቃላቶች እንዴትስ እሺ አሉህ? ያለ አንዳች በደሌ ክፋትህን ስታዘንብብኝ እንዳልሰማ አለፍኩህ:: አንተ ግን በዝምታዬ ውስጥ ያለውን ቅሬታ ልታይ አልቻልክም ምክንያቱም በተበላሸው ሀሳብህ ሰክረሀል የገዛ አንደበትህን መግዛት ተስኖሀል ራስህን ማወቅ ከብዶሀል::

አፈርኩልህ ሳልጠጋህ ስትገፋኝ ሳልስምህ ስትነክሰኝ አፈርኩልህ ተጠየፍኩህ ክብሬን እንዳትነካ ራኩህ:: ከአካሌም ከሀሳቤም ከመንፈሴም አገለልኩህ :: እኔ እኔ ነኝ አንተ ባሰላኸው ማልሰላ ስትገፋኝ ማልወድቅ በሚዛንህ ማልተመን ራሴ ነኝ::

ዝምታ አለማወቅ አይደለም ፀጥታ አለመረዳት አይደለም ጭጭታ ባዶነት አይደለም:: በዝምታ ውስጥ የሚንቦገቦግ ጥበብ በፀጥታ ውስጥ የሚያንፀባርቅ እውነት አለ:: ጭር ረጭ ባለበት ያልተሰማ ዜማ ይፈሳል:: እንደመብረቀ በሚያስደነግጠው አንደበትህ ተከፋው እንደ አውሎ

ንፋስ በሚጠራርገው ድፍረትህ አዘንኩ እንደ እሳት በሚለበልበው አይንህ ደማው፡፡ ግን ያ እኔነቴን አይነካውም ርጋታዬን አያናጋውም ከጉዞዬም አያስቆመኝም ሁሉ ነገር ነበር ሆኖ እስኪያልፍ ድረስ ግን አፍርልሃለው ምክንያቱም ድርጊቶችህ የሚገልጡት ያልተገነባ ማንነትህን እንጂ አጠገብህ ቆሜ የምታዘብህን እኔን አይደለምእና፡፡

ሰውረኝ

ታውቃለህ አቅሜን ታውቃለህ የማልችለውን እንደማትሰጠኝ እኔም አውቃለው ሆኖም አምኜም አውቄም እለምንሃለው ከፈተና ሰውረኝ ብዬ ፀሎት አቀርባለው:: አዎ ከጉያህ ውስጥ ደብቀኝ ሸሽገኝ ክፉን አታሳየኝ:: እንዲህ ብዬ እለምንሃለው ከክፉ ቀን ሸሽገህ አስመልጠኝ:: አንዳች ጥፋት ሳላይ አሳልፈኝ አሻግረኝ እልሀለው:: እኔ ምለምንህ ሰውረኝ ብዬ ነው አታሳየኝ ብዬ ነው አትፈትነኝ ብዬ ነው ሸሽገኝ ብዬ ነው ምክንያቱም አምላኬ ይሄን ማድረግ ትችላለህ:: ፍቅርህን አውቃለው ምረትህን አይቻለው ማዳንህን አግኝቻለው:: አምኜ እለምንሀለው ጠይቄም እቀበላለው::

ሀይልን አልጠይቅም መቻልን አልፈልግም መበርታትን አልሻም:: ትችላለህ እና ከፈተና ሁሉ ሰውረኝ እላለው በእጆችህ ሸፍነኝ እላለው ከጉያህ ደብቀኝ እልሃለው:: አምላኬ ሁሉን ቻይ ሉአላዊ አምላክ ነህ:: ስምህም ድንቅ መካር ሀያል አምላክ ነው የጌቶች ጌታ የነገስታት ነጉስ አልፋ እና ኦሜጋ አንተ ነህ:: ራሴን ንቄ ህያውነትህን መስክሬ ከፊትህ እገኛለው እጆችህን እሻለው ልመናዬንም አቀርባለው ሰውረኝ ሰውረኝ ሰውረኝ እላለው::

የታመኑ እጆችህ ምንኛ መልካም ናቸው ማዳንህ እንዴት ጥልቅ ነው:: ሁሉን ቻይ አምላክ ነህ ዘመን የማይሽህ ቃልህ የታመነ መንግስት የፀና ነው:: እን ከገባኝ ከተገለጠልኝ በላይ ነህ ስምህን ጠርቼ አላፍርም እና ዛሬም

ከፊትህ ቀርቤ ልመናዬን አሰማለው፡፡ ሰውረኝ ከፈተና ሁሉ አስመልጠኝ አሳልፈኝ አስችለኝ አድነኝ አስተምረኝ አቁመኝ፡፡

ተሰውሬም ግን ዝም አልልም አንደበቴን ለምስጋና አላቅቃለው፡፡ የተፈጠርኩት መስጋናን እንደ ንጹህ ምንጭ ለማፍለቅ ነው፡፡

አጠይቁኝ

እጄን ሳልዘረጋ የሞላልኝ እጁ

ልመና ሳላቀርብ ሳልጠና ከደጁ

እንደሸክላ ሰሪው አቡክቶ ለውሶ

ደግሞም የወደደኝ መልሶ መላልሶ

እሱ ባለቤቱ ጌታ ፈጣሪዬ

ምን ብዬ ልመልስ በእጆቹ ተስዬ

አዎ አጠይቁኝ ማነሽ አትበሉኝ

ስለተፈጥሮዬ ደርሶ አትሞግቱኝ

እኔ ሸክላ ሆኜ እሱ ባለቤቱ

ማንነቴ ምለው ምኔን ነው በሞቴ

ይልቅ ለወደደኝ ይሰዋ ምስጋና

በስራው ትክክል ኤልሻዳይ ነውና

ሙሽራዬ

ውዴ ሙሽራዬ

እረኛ ጌታዬ

እጄን ዘርግቻለው

እርዳታን እሻለው

ላይህ እጠማለው

ትናንትናም ዛሬም እጠብቅሃለው

ውዴ ሙሽራዬ

ሁሉን ባንተ ችዬ

ያበቃን ረስቼ

በቃልህ በርትቼ

አለሁኝ እላለው

ዛሬም አምንሃለው

ውዴ ሙሽራዬ

ሸክሜንም ጥዬ

ስምህን ይዣለው

በፍቅርህ ድኛለው

ባንተ እችላለው

አዲስ ቀን አያለው

ውዴ ሙሽራዬ

መከታ ጋሻዬ

ፍቅርህን አንግቼ

ዘመኑን ዋጅቼ

አለሁኝ አልፌ

ለአለም ተርፌ

ልከኛ

ፍርደ ገምድል ነበርኩ በአይን የምለካ

የጠላቴን ውድቀት አይቼ ምረካ

ጥፋት በመሰለኝ ትችት የምመዝዝ

የወደቀን ሁሉ አጥብቄ ማወግዝ

ፍርደ ገምድል ነበርኩ ጉድፍ የማወጣ

ያጠፋን ረጋሚ አልፎም የምቀጣ

ፅዩፍ ንፁህ መሳይ አዋቂ ጀብደኛ

ሀጥዕን ስገፉ ማሳጣው መፅናኛ

ዛሬ እኔም ደከምኩ አልቻልኩም ተሸነፍኩ

መሞከር ታከተኝ አቃተኝ ተማረኩ

ቆሜያለው ካልኩበት ከተደገፍኩበት

እያደር ወረድኩኝ ከፍ ከፍ ካልኩበት

ለካ

በሰፈሩት ቁና ለካ ይሰፈራል

ፍርድን ካዛቡበት ይግባኝ ይለመናል

ተረትተረት እውነት ከህይወት ሲቀዳ

ነፍስን ያረሰርስ መአዛው ፀአዳ

"ውዶች ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም" እናም ያለኝን አካፈልኩ ከወደዳችውት እሰየው ባትወዱትም እሰየው ነው